# የታክስ ጥሰትና የወንጀል ሃብት ህጋዊ ማስመሰል ወንጀል

በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ በማስመሰል ማቅረብ ወንጀል የተደራጁ እና ድንበር ተሻጋሪ ከሚባሉ ወንጀሎች ይመደባል። ወንጀሉ እንደ ወንጀል መቆጠር የተጀመረበት ጊዜ ሩቅ የማይባል በ20ኛዉ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እዉቅናና ትኩረት የተሰጠዉ ጉዳይ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ። የታክስ ጥሰት በመፈጸም የሚሰበሰብ ገንዘብ አንዱ የወንጀል አይነት በመሆን ይጠቀሳል። የታክስ ጥሰት የሚገኘውን የቆሸሸ ሃብት ምንጭን ለማድረቅ ደግሞ የታክስ አጣሪና መርማሪ አካለት/ ባለሙያዎች ትልቁን ድርሻ እንደሚይዙ ይታመናል።

ከዚህ አንፃር ታክስ የመሰብሰብና ማስከፈል ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት/አካላት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሃብት ህጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎች ጋር በተያየዘ አጠራጣሪ ግብይቶችን በመለየትና ሪፖርት በማድረግ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላሉ። በሂደቱ ውስጥ የታክስ አጣሪዎች፣ ኦዲተሮች እና መርማሪዎች የወንጀል ተግባራትን በመዋጋት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይሆንም ።በተለይ ደግሞ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሃብት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀሎች ባህሪና ተግባራት በማብራራት ለወንጀል መርማሪዎች ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ።

በመደበኛ የታክስ ኦዲት ሂደት ውስጥ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀሎችን የመለየት መንገድን ያመላክታሉ። በተጨማሪም የእነዚህ ወንጀሎች ምንጭ እና አፈፃፀም ዘዴዎቻቸውን በመግለፅ ለውጤታማ የወንጀሎቹ ልየታና መከላከል ምቹ ሁኔታ ፈጣሪም ናቸው። ስለዚህ የታክስ አጣሪና መርማሪ አካለት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሃብት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎች በመከላከል ሂደቱ ላይ ከፍተኛ ድርሻን የሚይዙ መሆኑን ልብ ይሏል።

ከዚህ አኳያ የተለያዩ አገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው የታክስ አስተዳደር ተቋማት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀሎች መከላከልና መቆጣጠር ላይ የተሰማሩ ተቋማት ጋር በትብብር በመስረት የፋይናንስ ወንጀሎችን በጋር የመከላከል ስራ ያከናውናሉ። የታክስ ማጣራት ስራ የሚያከናወኑ ባለሙያዎች እና የታክስ ኦዲተሮች በወንጀል ድርጊት የመነጨ ሃብት ህጋዊ የማስመሰል እና ሽብርተኝነተን በገንዘብ የመርዳትን ምልክት በመለየት የመጀመሪያ ናቸው።

ባለሙያዎቹ ከትምህርት ዝግጅታቸው እንዲሁም ከተሰማሩበት የስራ መስክና ባህሪ በመነሳት አጠራጣሪ ግብይቶችን መለየት ያስችላቸዋል።

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሃብትን ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት አደገኛ የወንጀል ጥሰቶች ናቸው። በመሆኑም ለህይወት መጥፋት፣ ለግለሰቦች በህይወት መኖር ሙብት ጥሰት ጭምር ይዳረጋሉ።

የታክስ አጣሪዎችና ኦዲተሮች ይህን የወንጀል ፍሬ ህጋዊ ማስመሰል ምንጭ ላይ ግልጽ ምስል በመያዝ አጠራጣሪ ግብይቶችን ለፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል በማቅረብ ወንጀሉን ለመዋጋት ሚናቸው ትልቅ ነው። በተጨማሪም ከታክስ ጥሰት የመነጨን ህገ-ወጥ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን በተሻለ የመለየት ዕድል አላቸው።

የታክስ አጣሪና መርማሪ አካለት ጤናማ ያልሆኑ ግብይቶችን መለየት የሚያግዛቸው ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህ መካከል ደግሞ ግብይት ለማከናወን የተንቀሳቀሰ፣ የተከማቸ ወይም ወጪ የተደረገ የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ፣ የሚታወቅ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሃብት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ስልቶች/መንገዶችን ተጠቅመው እንደሆነ፣ የገቢ/ሃብት ወይም/እና ካፒታል መጠን መጨመር፣ ከተገለፀው ገቢ መጠን ጋር የማይጣጠም የሃብት ጭማሪ መኖር፣ ያልተለመዱ የብድር ስምምነቶችና ድርጊቶች፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት እንቅስቃሴ መኖር ይጠቀሳሉ።

እነዚህ አመላካቾች ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር ሊያያዙ የሚችሉ ሲሆን፤ ገንዘቦችን ከበጎ አድራጎትና ለትርፍ ያልተቋቋሙ አካላት መሰብሰብ፤ የሚታወቁ ህጋዊ ማስመሰያ ስልቶች መጠቀማቸው፣ ግጭት ከሚበዛባቸው አከባቢዎች ገንዘብ ወይም ሌላ ሃብት ፍሰት መኖር በተለይም ጤናማ የማይመስሉ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች መኖር፣ ያልተለመደ ወይም ከሚጠበቀው የተለየ እንቅስቃሴ መኖር ወዘተ ሲኖሩ ጠለቅ ያለ ትንተና ማድረግና ጉዳዩን በአንክሮ መመልከት ተገቢ ይሆናል።

ይህን መሰረት በማድረግ የሚካሄደው ጠለቅ ያለ ትንተናና ቅኝት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ የወንጀል ድርጊቱን ለመሰወር/ለመደበቅ፣ ሃብቱን ለማንቀሳቀስ እና ለማከማቸት የሚደረጉ ሂደቶችን መለየት ይቻላል። የገንዘቡ ምንጭ ግልፅ አለመሆን፣ በጉዳዩ ውስጥ የተሳተፉ አካላት ግልጽ ካልሆኑ/በግልጽ የማይታወቁ ከሆኑ፣ የግብይት ሁኔታው ሪፖርት ከተደረገው የግለሰቡ የኋላ ታሪክ/ወይም ገቢ ጋር የማይጣጠም ከሆነ፣ ከቀረበው ግብይት ጋር የሚጣጠም ኢኮኖሚያዊ ወይም አሳማኝ ምክንያታዊ ትንታኔ የሌላው ከሆነ ከወንጀል ድርጊት የተገኘ ሃብት ጠቃሚ ምልክት አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

በአጠቃላይ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ/ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ጋር ግንኙነት ሊኖረው የሚችል ጤናማ ያልሆነ ግብይት የሃብቱን ምንጭና ፍሰት በሚመለከት ወንጀሉን ለመደበቅና ለማሳመን የሚደረጉ የተለያዩ መገለጫዎች ሊኖሩት ይችላሉ። እነዚህም ገንዘቡ ከለጋሽ ወይም ለትርፍ ካልተቋቋሙ ተቋማት የመሰብሰብ፤ ከግጭት አከባቢዎች ከፍ ያለ የገንዘብ ፍሰት መኖር፣ ጤናማ ያልሆነ ግብይት አመላካች ጉዳዮች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሃብት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ጋር፣ ከግለሰቡ፣ ከታክስ ተመላሽ ምርመራና ቅድመ-ኦዲት አመላካቾች፣ ከንግዱ ሁኔታ፣ ከዓለም አቀፍ ንግድ ባህሪ ወዘተ መመልከት ይቻላል።

ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትነ በሚመለከት ደግሞ የተለያዩ አመላካች ጉዳዮችን መመልከት ይቻላል። እነዚህም ከግለሰቡ፣ ከንግዱ ሁኔታ፣ ከበጎ አድራጎትና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፣ ከዲጂታል ክፍያዎች የመሳሰሉት ጋር ተያይዞ ካሉት አመላካቾች አንፃር መመልከትና መለየት ተገቢ ነው። በእርግጥ ከላይ የተቀመጡ ጉዳዮች ጥቅል በመሆናቸው በየራሳቸው ዝርዝር ጉዳዮች እንዳላቸው መገንዘብ ተገቢ ነው። በጥቅሉ ሲወሰድ ግን ታክስ አጣሪና መርማሪ እንዲሁም የታክስ ኦዲተሮች ጤናማ ያልሆነ ወይም ጤናማ የማይመስሉ የግብይት አይነቶችን በስራ ሂደታቸው ሲመለከቱ ለፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ሪፖርት በማድረግ በአገር ላይ ሊደርስ የሚችለውን ከፍተኛ ጉዳት በመዋጋት ረገድ ላቅ ያለ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል እነዚህን ጉዳዮች በአግባቡና በጥንቃቄ በመያዝ ማስተናገድ የሚያስችል የራሱ የውስጥ አሰራር አለው። ስለሆነም በዚህ መስክ የተሰማሩ ባለሙያዎች አጠራጣሪ ጉዳዮች ሲገጥማቸው ጥቆማ በመስጠት የአገርን የፋይናንስና ኢኮኖሚ ጤናማነት መጠበቅ ላይ የድርሻቸውን ማበርከት አለባቸው እንላለን።